IBO IB DIPLOMA PROGRAMME
PROGRAMME DU DIPLÔME DU BI
PROGRAMA DEL DIPLOMA DEL BI

# AMHARIC A1 – STANDARD LEVEL – PAPER 1
# AMHARIQUE A1 – NIVEAU MOYEN – ÉPREUVE 1
# AMHARE A1 – NIVEL MEDIO – PRUEBA 1

Tuesday 21 May 2002 (afternoon)
Mardi 21 mai 2002 (après-midi)
Martes 21 de mayo de 2002 (tarde)

1 hour 30 minutes / 1 heure 30 minutes / 1 hora 30 minutos

INSTRUCTIONS TO CANDIDATES

- Do not open this examination paper until instructed to do so.
- Write a commentary on one passage only. It is not compulsory for you to respond directly to the guiding questions provided. However, you may use them if you wish.

INSTRUCTIONS DESTINÉES AUX CANDIDATS

- Ne pas ouvrir cette épreuve avant d'y être autorisé.
- Rédiger un commentaire sur un seul des passages. Le commentaire ne doit pas nécessairement répondre aux questions d'orientation fournies. Vous pouvez toutefois les utiliser si vous le désirez.

INSTRUCCIONES PARA LOS ALUMNOS

- No abra esta prueba hasta que se lo autoricen.
- Escriba un comentario sobre un solo fragmento. No es obligatorio responder directamente a las preguntas que se ofrecen a modo de guía. Sin embargo, puede usarlas si lo desea.

ከሚከተሉት ምንባቦች አንዱን መርጠህ(ሽ) አስተያየትህን(ሽን) ስጥ(ስጪ)፡፡

1. (ሀ)

## ከነጣቂ ራቂ

ይገደሩብሻል...ይቃጠሩብሻል
ጉድሽን ሰምተሻል
ጠልፈው ሊወስዱሽ ነው...
እንጅፌ አሞራ
እነ ጭልፊት አፉ
አንዱ አንዱን ተጣራ
ዙሪያሽን ከበቡሽ...ድግሞ አሰፈሰፉ
ምንድነው? በያቸው...መነጠል ያለውድ
ያለ ክብር መዳር
ያለ አቅጣጫ መጓዝ...ተጠልፎ መወሰድ
አላግባብ መደፈር
ከድንግልናሽ ነው አይናቸው እነሱ
ከተሞሸርሽማ መች ተቀባሽ እሮ
ሊያባልጉሽ እንጂ ክብርሽን ሊገስሉ
አንዱ ካንዱ አብሮ...ያ ከዚህ ተማክሮ
እንኳንስ ተጠልፈው..
ከናት ተለይተው ተድረው ሲሄዱ
ሆድ ባር ባር ነው እሚለው
ግራ ነው መንገዱ
መዳር በወጉ ነው ጓዝ ጠቅልሎ መሄድ
እናት አባት ስሞ መርቆ ሸኝቶ
በሰው ፊት መዋረድ ቆሞ መንገዳገድ
የተጠለፈች ልጅ ክብሯ መች ተገኝቶ
ልጄ ተሸሸጊ..ደግሞም ተጠንቀቂ
ያለ ሎጋው ሸቦ...ያለ ሆማ አበባ
ክብርሽን አትስጪ..ራስሽን ጠብቂ
የመቸዋልና ግርግር ለሌባ፡፡

መቅደስ ጀምበሩ፥ <u>እኛ፥ 170 ግጥሞች</u>፥ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፥ 1990፡፡

በግጥሙ ውስጥ ጠለፋ እንደምን ቀርቧል?

ገጣሚዋ ለሴት ህፃናት የምትሰጠው ምክር ምንድነው? ምክሩስ በምን መልክ ቀርቧል?

የገጣሚዋን የቃላት ምርጫና ምስል የመፍጠር ችሎታ በሚመለከት አስተያየት ስጥ(ስጪ)።

ይህንን ግጥም ስታነብ(ቢ) ምን አይነት ስሜት አደረብህ(ሽ)?

1. (ለ)

ንቦች ክብብ ያደርጓችኋል፡፡ ከወደጓሮ መውጫ በኩል ትልቅ ባልዲ ይዞ ቆሻሻ ውሀ በዩ ውስጥ ለመድፋት ወጣ ብሎ ግራ ቀኙን የሚያማትር፣ ጠቆር ጉስቆል ያለ፣ ቁምጣ ሱሪ የለበሰ፣ ባቱ ፍልጥ መስሎ የጠጠረ፣ ፀጉሩ የተንጨባረረ ሰውዬ ያጋጥማችኋል፡፡ ጠጅ ከምትበጠብጥ አንዲት እዛው ቤት ካደገች ወፍራም (ደንደሮ) ሴት የሚወረወርበት ስድብ መሣይ ቀልድ ቢዘገንናችሁም የወትሮ ጠባያቸው ነውና እምብዛም አይክበዳችሁ፡፡

ለማናቸውም ጠጅ ቤት ልትገቡ ነውና እንዳትሰለቹ፡፡ ደሞ አስተያየት ከመስጠት ተቆጠቡ፡፡ ምክንያቱም «ፈጣሪዬ እንኳን ለዚህ አበቃኸኝ» ብለው የሚያመሰግኑ የሚመስሉ ጨዋ ጨዋ ሰዎች ስልክ እንጨትም ግንብም ጋ ቆመው ሽንት ያፈሳሉ፡፡ ለማኞች፣ ቆሎ ሻጮች፣ ልብስ አዟሪዎች፣ ዱርዬዎች... በሩን ከበው የቆሙበት የጠጅ ቤቱ መግቢያ ነውና አሁን ልትገቡ በሯ ላይ ናችሁ ማለት ነው፡፡ ብቻ በዩ መሸጋገሪያ ላይ ያለችውን የምታረገርግ ጣውላ በጥንቃቄ ልብ ብላችሁ ማየት አለባችሁ፡፡ በኋላ ስትወጡ ልትጥላችሁ ትችላለች —አታስተማምንም፡፡

ግቡ፣ ደርሳችኋል፡፡ ከዚያ በመረጣችሁት አግዳሚ «ወንበር» ላይ ቁጭ ስትሉ «ነወር፣ይንበሩ፣» የሚሉ ትሁት ሰዎች ያጋጥሟችኋል፡፡ «ነወር» መባባል የዕድሜ ገደብ የለውም፡፡ ዓይነ ስውር አባቱን ቤት ለማድረስ ከሚመጣ ልጅና ከቆሎ ሻጮች፣ ከልብስ አዟሪዎች በስተቀር ሁሉም ጠጅ ጠጪ የ«ነወር» ባለመብት ነው፡፡ ታዲያ ባንድ የሚያበቃ አይምሰላችሁ፡፡ ሽንት ቤት ስትመላለሱና ወይራ ጭስ አጨናብሷችሁ ስትመጡ ሁሉ ትሕትና አትነፈጉም፡፡ ከተቀመጣችሁ በኋላማ «ቆሎ ዝገኑ!» ስትባሉ ትዘግኑና ሳታስቡት እፊታችሁ ገጭ ያለውን አደይ አበባ የመሰለ ጠጅ በብርሌ ማንዶቅዶቅ ነው፡፡

ከዚያማ ጨዋታው ይመጣል:: በያይነቱ:: መቼም ጠጅ ቤት አሽሙር ሞልቷል:: ድንገት ከየት መጣ ሳትሉ «ኧረ ንቦ አትናደፊ!» የሚል ዘፈን አይሉት ንግግር የማላዘን ዓይነት ድምፅ ትሰማላችሁ:: ቆይ፣ ዝም በሉት:: ጠጅ ቀጂው እስኪሰማው ነው::

በዚህ ዓይነት ጨዋታችሁን መኮምኮማችሁን ትቀጥላላችሁ:: ከዛ ዓይናችሁን ወዲያ ወዲህ ስትማትሩ ብዙ ነገሮችን ታያላችሁ:: የቤቱ ጣራ ሩቅ ነው:: ኮርኒስ ቢኖረው ጠጪዎች የሚያድሙ ይመስል የትም ቢሆን የሰፋፊ ጠጅ ቤቶች ቆርቆሮ ባንድ በኩል እርቃኑን ነው የሚሆነው:: የጣራው መራቅ ግን ምክንያት ሳይኖረው አይቀርም— በመጠጡ ላይ ሌላ የፀሐይ ግለት ለመከላከል:: አሠራሩ የጋራዥ አይነት መምሰሉ ደሞ ሌላው ገጽታ ነው:: እንዲያውም ነፋስ ቢጤ ለማስገባት አልፎ አልፎ ድመቶች የሚረማመዱባቸው ክፍተቶች ይኖራሉ::

መስፍን ሃብተማርያም፥ <u>የሌሊት ድምፆች እና ሌሎችም ወጎች</u>፥ ሜጋ አሳታሚ ድርጅት፥ 1992::

በጽሑፉ ውስጥ ጠጅ ቤት እንደምን ተገልጿል?

ጠጅ ቤት ፈገግ በሚያሰኝ አቀራረብ መቅረቡ አስተዋጽአው ምንድነው?

ፀሐፊው በአንባቢው አመለካከት ላይ ተጽእኖ ለማሳደር የተጠቀመባቸው ሌሎች ቴክኒኮች ምንድናቸው?

የጽሑፉ ዋና ዋና ጭብጦች (መልእክቶች) ምንድናቸው?